የሰ/መ/ቁ. 64397

ጥር 01 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ አንዳርጌ እምሩ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ዘሀራ መሀመድ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ቴሌቭዥን ከነሲዲው ተጠሪ እገዛልሃለሁ በማለት ተቀብላኝ ዕቃውም ተገዝቶ ያልቀረበ ከመሆኑም በላይ ገንዘቡም አልተከፈለኝም በሚል የቀረበ ክስ ሲሆን የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቀበሌ 10/11/12 ማህበራዊ ፍርድ ቤት በአሁኑ አመልካች ከሳሽነት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረውም ክስ ተከሳሽ መስከረም 17 ቀን 2001 ዓ.ም. በከሳሽ ቤት መጥተው አንድ ባለ 21 ኢንች ሶኒ ቴሌቪዥን ከነሲዲው ቀረጡን ጨምሮ በብር 4750(አራት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ) ገዝቼ አመጣልሃለሁ ብለውኝ በምስክሮች ፊት ገንዘቡን ቆጥሬ ሰጥቼያቸው ቴሌቪዥኑን ያላስረከቡኝ ሲሆን ገንዘቡም እንዲሰጠኝ ብጠይቃቸው ወይም ዕቃውን እንዲያስረክቡኝ ብጠይቃቸው ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ዕቃውን እንዲያስረክቡኝ ወይም ገንዘቡን እንዲመልሱልኝ እንደዚሁም በክሱ ምክንያት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ጭምር እንዲከፍሉኝ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ በቀረበው ክስ ላይ ተከሳሽ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዙት መሰረት መጥሪያ ተልኮላቸው ለመቀበል ፍቃደኛ ያለመሆናቸውን ከሳሽ በቃለ መሓላ ማረጋገጣቸውን በማመልከቱ ጉዳዩ ተከሳሽ በሌሉበት እንዲታይ ትእዛዝ ተሰጥቶ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር ፍርድ ሰጥቷል፡፡ የሰጠውም የፍርድ ይዘት ተከሳሽ በቀረበው ክስ ላይ ቀርበው መልስ ያለመስጠታቸው የቀረበውን ክስ እንዳመኑ ስለሚቆጠር ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከወጪና ኪሳራ ጭምር እንዲከፍሉ በማለት በአሁኑ ተጠሪ ላይ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በቀጥታ ይግባኛቸውን ለከተማው አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የቀረበውን ቅሬታ ከመረመረ በኋላ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 337 መሰረት አጽንቷል፡፡ በዚህ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ቅሬታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን ተጠሪ ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በፍትሐ ብሔር ህግ ቁ. 2472(1)(2) መሰረት ከብር 500 (ብር አምስት መቶ) በላይ የሆነ ብድር በጽሑፍ፣ በፍርድ ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም ቃለ-መሓላ ካልሆነ በስተቀር በሰው ምስክር ማስረዳት እንደማይቻል፣ በተመሳሳይም ከብር 500 በላይ ከፍያለሁ በማለት የሚቀርበው ክርክር ይሄው ድንጋጌ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን በማመላከት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪን ከቀረበባቸው ክስ በነጻ በማሰናበት በአብላጫ ድምጽ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩም ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር በጽሑፍ ሰምተናል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ አመልካች ቴሌቪዥን እና ሲዲ ገዝተው እንዲያመጡላቸው ለተጠሪ የሰጡትን ብር 4750 (አራት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር) በሰነድ እንጂ በሰው ማስረጃ ማረጋገጥ አይቻልም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል የነበረ በመሆኑ ጉዳዩን ከዚሁ አኳያ ተመርምሮ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ጉዳዩን ስንመረምር የአሁን ተጠሪ በክሱ እንደተመለከተው ገንዘቡን የተቀበሉት ቴሌቪዢን እና ሲዲ ገዝቼ አመጣልሃለሁ በማለት እንጂ በብድር ምክንያት ያለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተመሳሳይም ተፈጻሚነት ያለው ከዚሁ ብድር ጋር በተያያዘ መልሼ ከፍያለው የሚል ተከራካሪን የሚመለከት እንጂ በዚህ ጉዳይ ላይ በግራ ቀኙ መካከል ብድርን መሰረት ያደረገ ክርክር በሌለበት ሁኔታ የፍትሐብሔር ህግ ቁ.2472 ን በመጥቀስ ከብር 500 በላይ የሆነን የገንዘብ መጠን በሰው ምስክር ማስረዳት አይቻልም ወደ ሚለው መደምደሚያ መድረሱ አግባብነት የሌለው እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ በአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት አነስተኛ ድምጽ አስቀምጦት የነበረው ሃሳብ አግባብነት የነበረው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ተጠሪ መጥሪያ ለመቀበል ፍቃደኛ ያለመሆናቸው ተገልጾ ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ በመስጠቱ የቀረበውን ክስ ከሳሽ በቆጠረው ምስክር ተከሳሽ ባይቀርቡም በመስማት እና ጉዳዩን በማጣራት ውሳኔ መስጠት ሲገባው የተጠሪ ያለመቅረብ ጉዳዩን እንዳመኑ የሚያስቆጥር ባለመሆኑ ክሱን እንዳመኑትት ይቆጠራል በማለት ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለው እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

ባጠቃላይ በግራ ቀኙ መካከል አከራካሪ የሆነው ጉዳይ ቴሌቪዢን እና ሲዲ ለመግዛት ተጠሪ 500 ብር የተቀበሉ መሆኑን እንጂ የብድር ገንዘብ ስለመሆኑ ባልተነሳበት ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሌለውን የብድር ውል እና ክፍያ የተመለከተን ድንጋጌ በመጥቀስ ከብር 500 (ብር አምስት መቶ) በላይ በሰው ምስክር ማስረዳት አይቻልም በማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰበር ሰሚው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የደረሰበት መደምደሚያ እንደዚሁም ጉዳዩን በመጀመሪያ ተመልክተው የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ተጠሪ ቀርበው መልስ ያለመስጠታቸው ወይም ጉዳዩ በሌሉበት በመታየት ክሱን እንደማመን ይቆጠራል በማለት የሰጠውም ውሳኔ በተመሳሳይ አግባብነት የሌለው እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ.14696 በቀን 07-04-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት፣የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ በፍርድ ቤት በመዝ.ቁ.04417 ህዳር 07 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቀበሌ 10/11/12 ማህበራዊ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ.016/03 መስከረም 27 ቀን 2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የተከሳሽ በአንድ ክስ ላይ ቀርቦ ያለመከራከር ወይም የጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት መታየት የቀረበው ክስ ክሱን ሊያስረዱልኝ ይችላሉ በማለት ከሳሽ በክሳቸው በመዘርዘር ያቀረቡትን

ምስክሮች ብቻ በመስማት እና ተገቢዉን ማጣራት በማድረግ ውሳኔ ከሚሰጥ ውጪ የተከሳሽ ያለመቅረብ ጉዳዩን እንዳመኑት ይቆጠራል በማለት በክሱ መሰረት ውሳኔ የሚሰጥበት አግባብ የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም አመልካች በክሱ ላይ የቆጠራቸው ምስክሮች ተሰምተው እና ለፍትህ አሰጣጡ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የማህበራዊ ፍርድ ቤቱ ያመነባቸውን ማስረጃዎች በመቀበል ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡

3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ